የ 6 ኛ ክፍል

የ 3 ኛ ተርም ኖት

3.4. የአፈር እና የውሃ ሀብት የመጠበቅና የመንከባከብ ዘዴዎች

- አፈር በተፈትሮ የሚገኝ የማያልቅ የተፈጥሮ ሀብት ከሆኑት አንዱ ነው፡፡
- አፈር የተለያዩ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ነገሮች በስባሽ ውህድ ነው፡፡
- አፈር በጥንቃቄ ካልተያዘ ለምነቱ ምርታማነቱ ሊቀንስና ሊሸረሸር ይችላል፡፡ ስለዚህ ሚከተሉት የአፈር ሀብት አያያዝና አጠባበቅ ዘዴዎችን መከተል አስፈላጊ ነው፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ድነና፡- ቀደም ሲል ደንን ሽፋን /የእፅዋት ሽፋን ያልነበሩበትን አካበባቢ አካባቢ ዛፍ ችግኞችን በመትከልና በመንከባከብ ስነ ምህዳሩን የመጠበቅን የአፈር ሀብት እንዳይሸረሸር ማድረግ/ የእንስሳት ምቹ መጠበቅ የአካባቢውን እንስሳት መተበቅ የዝናብ ሁኔታ አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ/ የተፈትሮ ሚዛን መጠበቅ ወ. ዘ. ተ የመጠበቅ ስርዓት ነው፡፡

ለ. ዳግም ድነና ፣ የጠፋውን ደን እንደገና መመለስ ማለት ነው፡፡

- ዳግም አካባቢው ለምነት ውብት እንደገና መመለስ ማለት ነው፡፡
- ምትክ የመተካት ሥርዓት ዘዴ ነው፡፡
- የእፅዋት /ደን/ ሽፋን ቀጣይነት እንዲኖረው የማድረግና የአፈር ሃብትና እንዲሁም ለዝናብና ለፀሐይ እንዳጋለጥ /እንዳይሸረሸር/ ይረዳል፡፡

ሐ. ጣምራ የደን እርሻ ፡-

ገበሬዎች ከእርሻ ስራዎች ጋር /ተግባራት ጋር/ ጎን ለጎን በእርሻ አካባቢው እና እርሻ ላይ በእርሻው ላይ ጉዳት የማያስከትሉ ሀገር በቀል ዛፎችን ይተክላሉ ይህ ስርዓት ጣምራ የደን እርሻ ይባላል፡፡ የዚህ ዘዴ ጠቀሜታ፡፡

- አፈር በንፋስ ሃይል እንዳይወሰድ ይረዳል
- የተፈጥሮ ሚዛን ይጠብቃል፡፡
- ለገበሬዎች ገቢን ያሳድጋል/ ከማሳደግ አንፃር ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡
- ለረዥም ጊዜ እና ለአጭር ጊዜ የሚከናወን ዘዴ ነው፡፡
- አፈር ለም እንዲሆን እና እንዳይሸረሸር

መ. የእርከን ሥራ

- የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ከሚወሰዱ ተግባራት አንዱ ነው ፡፡
- አፈር ዝናብ በሚበዛበት ወቅት በቀላሉ በዝናብ ውሃ /ጎርፍ/ እንዳወሰድ ይረዳል፡፡
  ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ በዋናነት እንደምሳከሌ የኮንሶ ህዝብ (ማህበረሰብ) ማንሳት ቻላል፡፡
  ነገር ግን ዛሬ ላይ በአብዛኛዎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ዛሬ ላይ የተለመደና በዋናነት የሚጠቀስ የአፈር ሀብት አያያዝና አጠባበቅ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡

እርከን የሚሰራው የመልክዓ ምድር ገፅታው ተዳፋት (ዳገታማ) በሆኑ አካባቢዎች አፈር በቀላሉ ሊሸረሸር በሚችሉ አካባቢዎች ድንጋይ ካብ ወደ ጎን በመስራት (ቦይ በመቆፈር) ጎርፍ ውሃን መከላከል የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡

ሠ. ከፍተኛ አካባቢዎች ወደ ጎን ማረስ (አግድም ማረስ)

ይህ የእርሻ ዘዴ የእርሻ ተግባር ሲካሄድ የሚፈጥሩትን መስመሮች ከላይ በዝናብ ወቅት እያሽቆለቆለ የሚወርደውን የጎርፍ ፍጥነት ይቀንሳል፡፡

የዝናብ ውሃ ቀስ በቀስ ወደ መሬት ውስጥ እንዲሰርግ ያደርጋል፡፡

ረ. <u>ዘር ማፈራረቅ እና ጥቅም</u>

- ✓ የአፈር መከላትን ይቀንሳል
- ✓ የአፈር ለምነትን ይጠብቃል
- ✓ ሰብል አጥፊ ነብሳትን ለመቆጣጠር ይረዳል።
- ✓ ኬሚካል መዳበሪያ መጠቀም ይቀንሳል
- ✓ በሽታዎች ለመከላከል ይረዳል።
- ✓ አረም ለመቆጣጠር ይረዳል።
- ✓ የተሸለ ምርት ለማግኘት ያስችላል።

ቀ. - ሰው ሰራሽ ማዳበሪያዎችን ያለ አግባብ መጠቀምን መቀነስ

- ሰው ሰራሽ ኬሚካል ማዳበሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም
- (የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን መጠቀም)

➢ <u>የውሃ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ዘዴዎች</u>

ሀ. <u>ውሃን ማቆር፡-</u> ለምሳሌ

- የዝናብ ውሃ
- የከርሰ ምድር ውሃ እንቅስቃሴ መገደብ
- በዝናብ ወቅት ከጣሪያ የሚወርድ ውሃን መሰብሰብ

ለ. ውሃን ብክለት መከላከልና ውሃ በካዮች

- ➢ ከኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚወጡ ዝቃጮች እና ኬሚካሎች
- ➢ ከቤት ውስጥ የሚወጡ ፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻዎች
- ➢ ኤነ ምድር (ከወንዝ አካባቢ መፀዳዳት)
- ➢ ከእንስሳት መመገቢያ ገንዳዎች ሚወጡ ቆሻሻዎች
- ➢ ሽንትቤቶች ከወንዝ ውሃ ጋር ማገናኘት
- ➢ ኬሚካል ማዳበሪያዎች

- <u>አየር በካዮች</u>

- ✓ የተፈጥሮ ዘይት /የድንጋይ ከሰል/ በሚቃጠልበት ወቅት
- ✓ የተለያዩ ትራንስፖርት ጭስ
- ✓ ከትልልቅ ኢንዱስትሪዎች የሚለቀቁ በካይ ጋዝና ጭስ
- ✓ ደረቅ ቆሻሻዎችን ማቃጠል (ሲቃጠሉ)
- ✓ ከደረቅ እና ፈሻስ ቆሻሻ የሚተን በካይ ጋዝ
- ✓ አቧራ እና የማድ ቤት (የኩሽና ጭስ)

⇒ <u>የመከላከያ ዘዴዎች</u>

- ❖ ከትላልቅ ኢንዱስትሪዎች የሚለቀቀውን ጭስ መቀነስ
- ❖ ደኖችን መንከባከብ የአካባቢውን ውበት መጠበቅ
- ❖ <u>ደንን</u> እና ዳግም ድነናን ተግባራዊ ማድረግ
- ❖ ታዳሽ (አማራጭ) ኃይል መተቀም
- ❖ ደረቅ ቆሻሻዎችን ከማቃተል እና ሌሎችን ኬሚካሎችን ከማቃጠል መቆጠብ
- ❖ የተለያዩ አስተማሪ የሆኑ ህጎችን እና ደንቦችን በማጽደቅ የአካባቢውን ብክለት የአየር ብክለት እና ውሃ ብክለትን ለመከላከል እንዲችል ህብረተሰቡን የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች ማስተማር እና ማስተዳደር።

3.5 <u>የኢትዮጵያ እና የምስራቅ አፍሪካ ብሔራዊ ፓርኮችና ጠቀሜታ።</u>

ብሔራዊ ፓርክ ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኝ የህዝብ መሬት (ይዞታ) ወይም ውሃ አካላት ናቸው። ብሔራዊ ፓርክ፡-

- ❖ ሥነ ምህዳርን
- ❖ የእፅዋት የእንስሳት እና የአእዋፋት ሀብትን
- ❖ የመሬት ገፅታዎችን
- ❖ የሥነ - ምህዳር ሂደት ውጤቶችን
- ❖ ታሪካዊ ስፍራዎችን

- ቅሪተ አካል መገኛ ስፍራዎችን የሚያጠቃልል ተለይተው እንዲጠበቁ የተከለሉ ቦታዎች ናቸው

➢ <u>የብሔራዊ ፓርክ አላማ እና ጠቀሜታ</u>

- ለህዝብ መዝናኛነት
- ለጥናት እና ምርምር
- ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር አመች እንዲሆን /ለቁጥጥር ምቹ እንዲሆን
- የእፅዋት የእንስሳትና የአእዋፋት ሀብት ለመጠበቅ
- ሥነ ምህዳሩን/መካነ ህይወት እንዲጠበቅ
- የተፈጥሮ ሚዛናዊ ሁኔታ የተጣጣመና እንዳይዛባ
- ለኢኮኖሚ /ለምጣኔ ሀብታዊ እድገት ታስቦ
- የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ስርዓት ቀጣይነት እንዲኖር ታስቦ

⟹ <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፓርኮች</u>

1. ሰሜን ተራሮች ብ.ፓ
2. አብጃታ ሻላ ሐይቆች
3. አዋሽ
4. ባሌ ተራሮች
5. ጋምቤላ ብ.ፓ
6. ማጎ
7. ነጭ ሳር ብ.ፓ
8. ኦሞ ብ.ፓ
9. ያንጉዲራሳ ብ.ፓ ናቸው

<u>ህብረተሰብ</u>

<u>የ **6** ኛ ክፍል የ **3** ኛ ተርም አክቲቪት ጥያቄ አንድ</u>

<u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ</u>

1. የጣምራ የደን እርሻ ጠቀሜታ አብራሩ።

____
____
____
____

2. ጣምራ የደን እርሻ ማለት ምን ማለት ነው?

____
____

3. ዘር ማፈራረቅ ጠቀሜታ ዘርዝር::

____
____
____

4. ሰው ሰራሽ ኬሚካል ማዳበሪያዎችን አለአግባብ መጠቀም የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅእኖ አብራሩ::

5. የውሃ ሀብት አያያዝና አጠባበቅ ዘዴዎችን ዘርዝር።

6. የውሃ ሀብት ብክለት እና ብክነት እንዴት መከላከል ይቻላል?

7. ብሔራዊ ፓርክ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኝ የህዝብ ሀብት ሲሆን ምን ምን ነገሮች ያጠቃልላል?

8. የድነና እና የዳግም ድነና ምንነት በመለየት ግለጽ።
ድነና፡- ________________
ዳግም ድነና፡- ________________

9. ከፍተኛ አካባቢዎችን ወደ ጎን ማረስ ምን ጥቅም አለው?

10. ዘር ማፈራረቅ የአፈር መከላትን ይቀንሳል ሲባል ምን ማለት ነው?

<u>የ 6 ኛ ክፍል ህብረተሰብ የ 3 ኛ ተርም የመጀመሪያው ወርክ ሽት</u>

<u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ /ጪ</u>

1. የአፈር ሀብት አያያዝና አጠባበቅ ዘዴዎች ቢያንስ አራቱን ጥቀስ

   1. ________________ 3. ________________

   2. ________________ 4. ________________

2. ዘር ማፈራረቅ ጠቀሜታዎች ቢያንስ ሁለቱን ግለጽ።

   1. ________________ 2. ________________

3. ጣምራ የደን እርሻ ማለት ምን ማለት ነው? ጠቀሜታው ምንድን ነው?

4. ታዳሽ ኃይል ማለት ምን ማለት ነው?

____
____

5.የአየር በካዮች ወስጥ ቢያንስ አራቱን ዘርዝር።

1. ____________________ 3. ____________________

2. ____________________ 4. ____________________

6. ብሔራዊ ፓርክ ምን ምን ነገሮች ይካተታል?

____________________ ____________________

____________________ ____________________

7.በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ ቢያንስ አራቱን ዘርዝር።

____________________ ____________________

____________________ ____________________

8. በኢትዮጵያ ውስጥ በእርከን ስራ የሚታወቀው የምን ህዝብ ነው? ______________

9. አፈር ምን ድን ነው?

____
____
____

10.የውሃ ሃብት አጠባበቅ አስፈላጊነት ዘርዝር።

____
____
____
____